የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፩
አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 51
ADDIS ABABA 20 August, 2007

ማ ው ጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፵፩/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ማዕደቂያ አዋጅ…. ገጽ ፫ሺ፯፻፴፬

CONTENTS

Proclamation No. 541/2007

Development Conservation and Utilization of Wildlife Proclamation …. Page 3734

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፵፩/፲፱፻፺፱

## የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አ ዋ ጅ

የዱር እንስሳት ሀብት ባልተቀናጀና አለአግባብ በሆነ አጠቃቀም ምክንያት እየተመናመነ በመምጣቱና ህልውናው አደጋ ላይ መውደቁ፤

እስከዛሬ ለዱር እንስሳት እየተደረገ ያለው ጥበቃና እንክብካቤ ውጤታማ ሆኖ ባለመገኘቱ፤

በጥበቃ ቦታዎች አካባቢ የሚኖረውን ሕብረተሰብና የግል ባለሃብቶችን በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ጠቀሜታው የጎላ ስለሆነ፤

ቀደም ብለው የወጡትና እስከዛሬ የሚሠራባቸው አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የጊዜውን ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘቡና አሁን ያለውን ፌዴራላዊ ሥርዓት የተከተሉ ባለመሆናቸው፤

ከዱር እንስሳት ሀብት የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥቅም በማጎልበት ለድህነት ቅነሳው ስትራቴጂ የሚኖረውን ሚና ማሳደግ የተገባ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግሥት አንቀጽ ፶፭ /፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO.541/2007.

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE DEVELOPMENT CONSERVATION AND UTILIZATION OF WILDLIFE

**WHEREAS,** unplanned and inappropriate utilizeation of wildlife has resulted in their depletion and endangered existence;

**WHEREAS,** the conservation of wildlife undertaken so far is not productive;

**WHEREAS,** allowing local communities residing around conservation areas and private investors to actively participate in wildlife development, conservation and utilization has significant value;

**WHEREAS,** the proclamations, regulations and directives issued previously and still in force are not in line with the existing objective reality and the present state structure;

**WHEREAS,** it is appropriate to enhance the contribution of the wildlife sector towards poverty reduction strategy by maximizing the economic and social benefit to be derived from the wildlife resource;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ፭፻፵፩/፲፱፻፺፱” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩/ “የዱር እንስሳት” ማለት ከቤት እንስሳ በስተቀር በሕይወት ያለ ወይም የሞተ የጀርባ አጥንት ያለው ወይም የሌለው እንስሳ ነው፡፤

፪/ “የዱር እንስሳት ሀብት” ማለት በኢትዮጵያ የሚገኙ የዱር እንስሳት ማለት ሲሆን ከአገር ወደ አገር የሚሰደዱና በጊዜያዊ መልክ በኢትዮጵያ የሚኖሩትን ዝርያዎች ይጨምራል፤

፫/ “የዱር እንስሳ ውጤት” ማለት የማንኛውም የዱር እንስሳ ናሙና ወይም የእንስሳው አካል፣ እንቁላል፣ እጭ፣ ዝባድ፣ ቀንድ፣ ጥርስ፣ ጥፍር፣ ቆዳ፣ ሥጋ፣ ጠጉር፣ ላባ ወይም ጎፍላው ሲሆን ከእነዚህ የተሠሩ ውጤቶችንና ከእንስሳው መኖሪያ አካባቢ የተገኙትን የወፍ ጎጆ፣ እንጨት፣ ሣር፣ ልጣጭ፣ አበባ፣ ማርና የመሳሰሉትን ይጨምራል፤

፬/ “የዱር እንሰሳ የመኖሪያ አካባቢ” ማለት የየብስ፣ የውሃ አካል ወይም ሁለቱንም የሚያካትት ሆኖ የዱር እንስሳት የሚኖሩበት የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታ ወይም ከጥበቃ ቦታ ውጪ ያለ ስፍራ ነው፤

፭/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ መሠረት ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው ሰው ነው፤

፮/ “ራንች” ማለት በግዥ የተገኙ ወይም ከዱር የተሰበሰቡ የዱር እንስሳትን ተንከባክቦ በማሳደግ ጥቅም ላይ ለማዋል የተከለለ ሥፍራ ነው፤

፯/ “የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታ” ማለት ለዱር እንስሳት ጥበቃ የተከለለ ሥፍራ ሲሆን ብሔራዊ የዱር እንስሳት ጥበቃ ፓርክን፣ የዱር እንስሳት መጠለያዎችን፣ የዱር እንስሳት ጥበቃ ክልሎችን እና የዱር እንስሳት የቁጥጥር አደን ቀበሌዎችን ይጨምራል፤

፰/ “የብሔራዊ ፓርክ ” ማለት የዱር እንስሳትንና ከነዚሁ ጋር የተያያዙትን ሐይቆችንና ሌሎች በውሃ የተሸፈኑ ሥፍራዎችን ጨምሮ ለአካባቢው ውበትና ለሳይንሳዊ እውቀት የሚረዱትን የተፈጥሮ ሃብቶች ለመጠበቅ የሚከለል ቦታ ነው፤

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the “Development Conservation and Utilization of Wildlife Proclamation No. 541/2007.”

### 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ “wildlife” means any live or dead vertebrate or invertebrate animal, other than domestic animal;

2/ “wildlife resource” means wild animals found in Ethiopia and includes those species migrating from country to country and temporarily staying in Ethiopia;

3/ “wildlife product” means any sample of wild animal or its body part like, egg, embryo, horn, tooth, nail, skin, meat, hair, feather or trophy and includes products made thereof as well as bird nest, wood, grass, bark, flower, honey and the like obtained from the habitat of the wildlife;

4/ “Wildlife habitat” means as area with in or out of the wildlife conservation area, in which wild life inhabits and includes land, water bodies or both.

5/ “Person” means any natural or juridical person.

6/ “Ranch” means an area designated for the conservation and raising of purchased or collected wildlife for latter use.

7/ “wildlife conservation area” means an area designated for the conservation of wildlife and includes national wildlife conservation parks, wildlife sanctuaries, wildlife reserves and wildlife controlled hunting areas;

8/ “national park” means an area designated to conserve wildlife and associated natural resources to preserve the scenic and scientific value of the area which may include lakes and other aquatic areas;

፱/ “የዱር እንስሳት መጠለያ” ማለት አንዱ ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው የዱር እንስሳት ጥበቃ የሚከለል ሥፍራ ነው፤

፲/ “የዱር እንስሳት ጥብቅ ክልል” ማለት ለዱር እንስሳት ጥበቃ የሚከለል ሥፍራ ሆኖ ስፍራው ለዱር እንስሳት ጥብቃ ከመከለሉ በፊት በክልሉ ውስጥ ሰፍረው የነበሩ ሰዎች የዱር እንስሳቱን እየተንከባከቡ በቦታው እንዲኖሩ የሚፈቀድበት የጥበቃ ቦታ ነው፤

፲፩/ “የዱር እንስሳት የቁጥጥር አደን ቀበሌ” ማለት ለዱር እንስሳት ጥበቃ የሚከለልና ቁጥጥር እየተደረገ ሕጋዊ አደን የሚካሄድበት ሥፍራ ነው፤

፲፪/ “የዱር እንስሳት ንግድ ” ማለት የዱር እንስሳትን ወይም የዱር እንስሳት ውጤቶችን ወደውጭ መላክ ወደአገር ውስጥ ማስገባት መልሶ ወደውጭ መላክ ወይም እነዚህኑ የሚመለከት ማንኛውም ዓይነት የንግድ ልውውጥ ነው፤

፲፫/ “የዱር እንስሳት ቁጥጥር ሠራተኛ” ማለት የዱር እንስሳትና የዱር እንስሳት ውጤቶችን በሚመለከት የሚፈጸሙ ሕገ ወጥ ድርጊቶችን እንዲቆጣጠር በሚኒስቴሩ ወይም በሚመለከተው የክልል መንግሥት አካል የተመደበ ሠራተኛ ነው፤

፲፬/ “ማደን” ማለት የዱር እንስሳትን ለመግደል፣ ለማቁሰል፣ ለማጥፋት፣ ለማስፈራራት፣ ለማባረር፣ ለመያዝ፣ ለማጥመድ ወይም የዱር እንስሳት ላባ ወይም እንቁላል ለመውሰድ የሚወሰድ እርምጃ ወይም እንቅስቃሴ ነው፤

፲፭/ “መሣሪያ” ማለት የዱር እንስሳትን ለመግደል፣ ለመያዝ ወይም እንዳያመልጡ ለማድረግ የሚጠቀሙበት ጥይት የሚተኩስ መሣሪያ፣ ዳርት ጋን፣ ተወርዋሪ ሚሳየል፣ ፈንጂ፣ ቀስት፣ ዱላ፣ ስለት፣ ወጥመድ፣ መረብ፣ ጉድጓድ፣ መርዝ፣ ኬሚካል፣ ወይም ሌላ ማንኛውም ለዚህ ተግባር የሚውል መገልገያ ነው፣

፲፮/ “የአየር መንኮራኩር” ማለት በሰው ወይም ያለ ሰው የሚንቀሳቀስ ሆኖ በሞተር ኃይል በአየር ላይ በሚነዳ አካል ብቻ ሳይወሰን ማናቸውም አይሮፕላን፣ ሄሊኮፕተር፣ በአየር ላይ ተንሳፋፊ አካል፣ ነው፤

፲፯/ “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የግብርናና የገጠር ልማት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

9/ “wildlife sanctuary” means an area designated to conserve one or more species of wildlife that require high conservation priority;

10/ “wildlife reserve” means an area designated to conserve wildlife where indigenous local communities are allowed to live together with and conserve the wildlife;

11/ “wildlife controlled hunting area” means an area designated to conserve wildlife and to carry out legal and controlled hunting;

12/ “wildlife trade” means the import, export or re-export of wildlife or their products or any kind of business transaction related thereto;

13/ “wildlife anti-poaching officer” means an officer assigned by the Ministry or the concerned regional government organ to control illegal acts to be committed against wildlife and wildlife products;

14/ “hunting” means any measure or action taken to kill, wound, eliminate, scare, chase, capture or trap a wild animal or take an egg or feather of same;

15/ “weapon” means firearm, dart-gun, missile, explosives, bow and arrow, stick, sword, trap, net, holes, poison, chemical or any other instrument used to kill, capture or disable wild animals;

16/ “aircraft” means any type of airplane, helicopter, airship whether or not controlled or directed by human agency and without being limited to devices flown by automotive power;

17/ “Ministry” or “Minister” means the Ministry or Minister of Agriculture and Rural Development, respectively;

፲፰/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ የተመለከተውን ማንኛውንም ክልል እና አዲስ አበባንና የድሬዳዋ መስተዳድርን ይጨምራል፡፡

፫. <u>ዓላማ</u>

የዚህ አዋጅ ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

፩/ የኢትዮጵያን የዱር እንስሳት ሀብት መጠበቅ፣ መንከባከብ፣ ማልማትና በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል፤

፪/ የዱር እንስሳት ሀብትን አጠባበቅ፣ እንክብካቤና አጠቃቀም በሚመለከት መንግሥት በዓለም ዓቀፍ ስምምቶች መሠረት የገባቸውን ግዴታዎች ለመፈጸም እንዲችል ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

፫/ በዱር እንስሳት ሀብት ላይ የተመሠረተ ቱሪዝም እንዲስፋፋና ኢንቬስትመንት እንዲበረታታ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፡፡

## ክፍል ሁለት
## <u>የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችና የሕጋዊ አደን እንቅስቃሴዎች</u>

፬. <u>በፌዴራል መንግሥት የሚሰየሙና የሚተዳደሩ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች</u>

፩/ የሚከተሉት የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች በፌዴራል መንግሥት የሚሰየሙና የሚተዳደሩ ይሆናሉ፤

ሀ) ከፍተኛ የዱር እንስሳት ብዝሀ ሕይወት ስብጥር ኖሯቸው አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ወካይ ምህዳረ ቀጠናዎች የያዙ ብሔራዊ ፓርኮች፤

ለ) አገሪቱ በብቸኛ ባለቤትነት የምትታወቅባቸውና ለእልቂት የተቃረቡ ዝርያዎች መኖሪያ የሆኑ ብሔራዊ ፓርኮችና የዱር እንስሳት መጠለያዎች፤

ሐ) በመልክአ ምድር አቀማመጣቸው በሁለትና ከዚያም በላይ ባሉ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ ማናቸውም የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች፤ እና

18/ "region" means any region referred to in Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes Addis Ababa and Diredawa Administration.

**3. Objectives**

This Proclamation shall have the following major objectives:

1/ to conserve, manage, develop and properly utilize the wildlife resources of Ethiopia;

2/ to create conditions necessary for discharging government obligations assumed under treaties regarding the conservation, development, and utilization of wildlife;

3/ to promote wildlife-based tourism and to encourage private investment.

## PART TWO
## WILDLIFE CONSERVATION AREAS AND HUNTING ACTIVITIES

**4. Wildlife Conservation Areas to be Designated and Administered by the Federal Government**

1/ The following wildlife conservation areas shall be designated and administered by the Federal Government:

a) national parks that are nationally and globally significant and known to have representative ecological zones and embrace immense diversity of wildlife;

b) national parks and wildlife sanctuaries that are inhabited by the country's endemic and endangered species;

c) any wildlife conservation areas geographically situated within two or more regions;

መ) ከጎረቤት አገሮች ጋር በስምምት የሚቋቋሙ ማናቸውም የድንበር ዘለል የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች የሚሰየሙት ሚኒስቴሩ በሚያቀርበው ሃሳብ መሠረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይሆናል፡፡

**፭. በክልሎች የሚሰየሙና የሚተዳደሩ የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በፌዴራል መንግሥት እንዲሰየሙና እንዲተዳደሩ ከሚደረጉት በስተቀር ብሔራዊ ፓርኮች፣ የዱር እንስሳት መጠለያዎች፣ የዱር እንስሳት ጥብቅ ክልሎች፣ እና የዱር እንስሳት የቁጥጥር አደን ቀበሌዎች፣ የሚሰየሙትና የሚተዳደሩት ለክልሎች ይሆናል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች የሚሰየሙት ክልሎች በሚያወጧቸው ሕጎች ይሆናል፡፡

**፮. በግል ባለሃብቶች የሚተዳደሩ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች**

የግል ባለሃብቶች ከፌዴራል መንግሥትና ከሚመለከታቸው ክልሎች ጋር በሚያደርጓቸው የኮንሴሽን ውሎች መሠረት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ እና ፭ የተመለከቱትን የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች እንዲያስተዳድሩ ሊፈቀድላቸው ይችላል፡፡

**፯. በአካባቢ ሕብረተሰብ የሚተዳደሩ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬፣ ፭ እና ፮ ከተመለከቱት የጥበቃ ቦታዎች ውጭ የሚገኙ የዱር እንስሳት መኖሪያ አካባቢዎች በአካባቢው ሕብረተሰብ እንዲተዳደሩ በሚመለከታቸው ክልሎች ሊፈቀድ ይችላል፡፡

**፰. የአደን ፈቃድ**

፩/ ሚኒስቴሩ ወይም የሚመለከተው የክልል አካል ተግባሩን ለማከናወን በሚያደርገው ሂደት ምክንያት ከሚፈጽመው አደን በስተቀር ማንኛውም ሰው የአደን ፈቃድ ሳይዝ የዱር እንስሳት ማደን የተከለከለ ነው፡፡

፪/ የአደን ፈቃድ የሚሰጥበት፣ የሚታደስበት፣ የሚታገድበትና የሚሠረዝበት ሁኔታ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

d) any trans-boundary wildlife conservation areas that may be established in accordance with agreements with neighboring countries;

2/ The wildlife conservation areas referred to in Sub-Article (1) of this Article shall be designated by regulations to be issued by the Council of Ministers upon the recommendation of the Ministry.

**5. Wildlife Conservation Areas to be Designated and Administered by Regions**

1/ unless designated and administered by the federal Government pursuant to Article 4 Sub-Article (1) of this Proclamation, national parks, wildlife sanctuaries, Wildlife reserves and wildlife controlled hunting areas shall be designated and administered by regions.

2/ The wildlife conservation areas referred to in Sub-Article (1) of this Article shall be designated by legislation of the regions

**6. Wildlife Conservation Areas to be Administered by Private Investors**

Private investors may be authorized to administer the wildlife conservation areas referred to in Article 4 and 5 of this Proclamation by concession agreements to be concluded with the Federal Government and the concerned regions.

**7. Wildlife Conservation Areas to be Administered by Local Communities**

Wildlife habitats other than the conservation areas referred to in Articles, 4, 5, and 6 of this Proclamation may be authorized by the concerned regions to be administered by the local communities.

**8. Hunting Permit**

1/ No person, other than the Ministry or the concerned regional organ in the discharge of their duties, may hunt any game animal unless he is in possession of a hunting permit.

2/ The conditions applicable for the granting, renewal, suspension and revocation of hunting permits shall be determined by regulations and directives issued under this Proclamation.

፫/ ሚኒስቴሩ አደንንና የአደን ዘዴዎችን በሚመለከት ደንብ ያወጣል፡፡

**፱. ለሳይንሳዊ ተግባር የዱር እንስሳትን ወይም ውጤቶቻቸውን የመሰብሰብ ፈቃድ**

፩/ ከታወቀ የሳይንስ ተቋም የተጻፈ የድጋፍ ደብዳቤ በመያዝ የዱር እንስሳት ወይም ውጤት ለመሰብሰብና ለሳይንሳዊ ተግባር ወይም ትምህርት ለማዋል ለሚጠይቅ አመልካች ሚኒስቴሩ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተውን ፈቃድ የሚሰጠው ከዚህ አዋጅና የዱር እንስሳት ጥበቃን ከሚመለከቱ ሌሎች ሕጎችና ደንቦች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ኤኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችና ጥቅሞች

**፲. ኤኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ**

፩/ በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታ ውስጥ የሚደረግ ማንኛውም ኤኮኖሚያዊ የሥራ እንቅስቃሴ የዚህን አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን ድንጋጌዎች በማይቃረን ሁኔታ መካሄድ አለበት፡፡

፪/ ከዱር እንስሳት ሃብት አጠቃቀም የሚገኘውን ገቢ የፌዴራልና የክልል መንግሥታት የሚጋሩበት መንገድና የአካባቢው ሕብረተሰብ ተጠቃሚ የሚሆንበት ስልት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

**፲፩. በዱር እንስሳት ሀብት ላይ የተመሠረተ ቱሪዝም**

፩/ ሚኒስቴሩና ክልሎች አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በዱር እንስሳት ሀብት ላይ የተመሠረቱ የቱሪዝም ኢንቬስትመንቶችን ያበረታታሉ፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ፣ ለክልሎችና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥም ሆነ ከእነሱ ውጪ የሚከናወን የኢኮ-ቱሪዝም ልማት የአካባቢውን ሥነ-ምህዳራዊ ደህንነት እንዳይናጋ ያደርጋሉ፡፡

3/ The Ministry shall issue regulations pertaining to appropriate hunting and hunting methods.

**9. Permit for Collection of Wildlife or Wildlife Products for Scientific Purposes**

1/ The Ministry may grant permit to an applicant in possession of a recommendation letter from a recognized scientific institution for collecting wildlife or their products for scientific or academic purpose.

2/ The Ministry shall grant the permit referred to in Sub-Article (1) of this Article in accordance with directives issued by it in conformity with the provisions of this Proclamation and other laws and regulations pertaining to wildlife conservation..

## PART THREE
## ECONOMIC ACTIVITIES AND BENEFITS

**10. Economic Activities**

1/ Any economic activity to be undertaken within a wildlife conservation area shall be carried out in accordance with this Proclamation and regulations and directives to be issued hereunder.

2/ The mechanism whereby the Federal and Regional Governments, may share the profits derived from the utilization of wildlife resources and the mathods by which the community maybe benefited shall be determined by regulations to be issued under this Proclamation.

**11. Wildlife Resource Based Tourism**

1/ The Ministry and regions shall, in collaboration with the relevant bodies, promote investment in wildlife-based tourism.

2/ The Ministry, for Regions and other concerned bodies, shall ensure that development activities to be undertaken in or outside of wildlife conservation areas shall be carried out in such manner that the well-being of the ecosystem of the areas are not disturbed.

## ፲፪. በዱር እንስሳትና ውጤቶቻቸው ስለመነገድ

፩/ እንደአግባቡ ከሚኒስቴሩ ወይም ከሚመለከተው የክልል አካል በተገኘ ፈቃድ መሠረት ካልሆነ በስተቀር፣

ሀ) በዱር እንስሳትና በዱር እንስሳት ውጤት የመነገድ ተግባር ማካሄድ፣

ለ) ማንኛውንም የተዘጋጀ ወይም ያልተዘጋጀ የዱር እንስሳት ውጤት በባለቤትነት መያዝ፣ መሸጥ፣ ማስተላለፍ፣ ወደ ሌላ አገር መላክ ወይም ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፣ የተከለከለ ነው፡፡

፪/ ሚኒስቴሩና የሚመለከታቸው የክልል አካላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተጠቀሰውን ፈቃድ የሚሰጡት በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲሁም አገሪቱ አባል በሆነችባቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የተደነገጉትን በመከተል ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፲፫. የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች ከተሰጡት በተጨማሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩/ የዱር እንስሳት ሀብት ልማትን፣ ጥበቃንና አጠቃቀምን በተመለከተ ፖሊሲና የሕግ ረቂቅ እያዘጋጀ ለመንግሥት ያቀርባል፤ ሲፈቀዱም ተግባር ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፬ መሠረት የተቋቋሙትን የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን ያለማል፣ ያስተዳድራል፣ ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈጸሙባቸው ይከላከላል፤

፫/ በውጭ ቱሪስቶች ለሚካሄድ አደን ፈቃድ ይሰጣል፤

፬/ ማናቸውንም የዱር እንስሳት ወይም የዱር እንስሳት ውጤቶችን ከአገር ለማስወጣት ወይም ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚያስችል ፈቃድና የጤና ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

፭/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋሙ የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ዓለም አቀፋዊ መስፈርት ማሟላታቸውን በማረጋገጥ በዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ሕብረት ያስመዘግባል፣ እነዚህኑ መስፈርቶች ጠብቀው መተዳደራቸውን ይከታተላል፤

## 12. Trading in wildlife and their Products

1/ The following are prohibited unless a permit is obtained from the Ministry or the concerned regional organs, as appropriate:

a) Any activity of trade in wildlife and their products;

b) the ownership, sale, transfer, export or import of any processed or unprocessed wildlife product.

2/ The Ministry and the concerned regional organs may issue permits pursuant to Sub-Article (1) of this Article in compliance with the provisions of this Proclamation, regulations and directives issued hereunder and treaties to which Ethiopia is a party.

## PART FOUR
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 13. Powers and duties of the Ministry

The Ministry shall, in addition to those given to it under other provisions of this Proclamation, have the powers and duties to:

1/ prepare and present to the government draft policy and laws relating to the development, conservation and utilization of wildlife; and follow up the implementation of same upon approval;

2/ develop and administer wildlife conservation areas established in accordance with Article 4 of this Proclamation and control illegal activities to be committed in relation thereto;

3/ issue hunting permits to foreign tourists;

4/ issue permits and health certificates to export and import any wildlife or wildlife products;

5/ ensure that wildlife conservation areas established in accordance with this Proclamation meet international standards with a view to facilitating their registration by the International Union for Conservation of Nature, and follow up their administration accordingly;

፮/ ለዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ የቴክኒክ ዕርዳታና ሌላም ድጋፍ ሊሰጡ ከሚችሉ ወገኖች ጋር ዓለም አቀፍ ግንኙነት ይመሠርታል፤

፯/ ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በተግባር እንዲፈጸሙ ያደርጋል፤ አፈጻጸማቸውንም በተመለከተ ለሚመለከታቸው ዓለም አቀፍ ተቋማት በየጊዜው ሪፖርት እያዘጋጀ ያስተላልፋል፤

፰/ የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀምን በሚመለከት ጥናትና የሥልጠና ፕሮግራም ያካሂዳል፤ ወቅታዊ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያቀነባብራል፣ ለተጠቃሚዎች ያሠራጫል፤

፱/ ለክልሎች በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ረገድ አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤

፲/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሥልጣንና ተግባሩን ለሌሎች የፌዴራልና የክልል መንግሥት አካላት በውክልና ይሰጣል፡፡

፲፩/ በዱር እንሰሳት ጥበቃ ቦታዎችም ሆነ ከጥበቃ ቦታዎች ውጪ የሚገኙ የዱር እንስሳት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ በሽታዎችን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል

፲፪/ ከፌዴራል መንግሥት ጋር በተገባ የኮንሴሽን ውል መሠረት በግል ባለሀብቶች የሚተዳደሩትን የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን ይቆጣጠራል።

## ፲፬. <u>የክልሎች ሥልጣንና ተግባር</u>

ክልሎች በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች ከተሰጧቸው በተጨማሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሯቸዋል፤

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ መሠረት የተቋቋሙትን የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ያለማሉ፣ ያስተዳድራሉ፤

፪/ በሚያስተዳድሯቸው የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችና ከዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውጭ የሚገኙት የዱር እንስሳት ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈጸሙባቸው ይከላከላሉ፤ በፌዴራል መንግሥት በሚተዳደሩ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈጸሙ በመከላከል ረገድም አስፈጊ ውን ድጋፍ ያደርጋሉ፤

፫/ በግል ባለሀብቶችና በአካባቢ ሕብረተሰብ የሚተዳሩትን የዱር እንስሳት የጥበቃ ቦታዎች ይቆጣጠራሉ፤

6/ establish international relations with all bodies having the potential of providing technical assistance and other aid for wildlife development and conservation;

7/ ensure the implementation of treaties to which Ethiopia is a party and compile and submit periodical reports to the concerned international institutions;

8/ conduct research and training programs and collect, process and provide to users up-to-date information on wildlife development, conservation and utilization;

9/ provide support to regions with respect to the development and conservation of wildlife;

10/ delegate its powers and duties to other federal and regional government organs where necessary.

11/ Prevent and control incidents of wildlife diseases with in or outside of conservation areas

12/ Supervise wildlife conservation areas administered by private investors in accordance with concession agreements entered with the Federal Government.

## 14. Powers and Duties of Regions

Regions shall, in addition to those given to them under other provisions of this Proclamation, have the powers and duties to:

1/ develop and administer wildlife conservation areas established pursuant to Article 5 of this Proclamation;

2/ control illegal activities to be committed against wildlife in conservation areas administered by them and outside of conservation areas; and provide the necessary support in controlling such illegal activities in relation to wildlife conservation areas administered by the Federal Government;

3/ supervise wildlife conservation areas administered by private investors and local communities;

፬/ በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችም ሆነ ከጥበቃ ቦታዎች ውጪ በሚገኙ የዱር እንስሳት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ በሽታዎችን ይከላከላሉ፣ ይቆጣጠራሉ፣ ከአቅም በላይ ሲሆን ለሚኒስቴሩ ያሳውቃሉ፤

፭/ የዱር እንስሳት እርባታና ራንች ፈቃድ ይሰጣሉ፣ ይቆጣጠራሉ፤

፮/ በሰው ሕይወትና ንብረት ላይ አደጋ በሚያደርሱ የዱር እንስሳት ላይ ተገቢውን ጥናት በማካሄድ ችግሩ የሚቃለልበትንና የሚወገድበትን እርምጃ ይወስዳሉ፤ ከአቅም በላይ ሲሆን ለሚኒስቴሩ ያቀርባሉ፤

፯/ ከውጭ ቱሪስቶች በስተቀር በሌሎች ሰዎች ለሚካሄድ አደን ፈቃድ ይሰጣሉ፤

፰/ የዱር እንስሳትና የዱር እንስሳት ውጤቶች በባለቤትነት ለመያዝ፣ ለማስተላለፍና በአገር ውስጥ ለመሸጥ የሚያስችል ፈቃድ ይሰጣሉ፡፡

## ፲፭. የዱር እንስሳት ቁጥጥር ሠራተኛ ሥልጣን

የዱር እንስሳት ቁጥጥር ሠራተኛ የሚከተለው ሥልጣን ይኖረዋል፤

፩/ የዱር እንስሳት ወይም የዱር እንስሳት ውጤት ይዞ የተገኘውን ማንኛውንም ሰው እነዚህኑ ለመያዝ ያስቻለውን ሕጋዊ ፈቃድ እንዲያሳይ የመጠየቅ፤

፪/ ሕግን በመተላለፍ በይዞታ ሥር የተደረጉ የዱር እንስሳት ወይም የዱር እንስሳት ውጤቶች ተደብቀዋል ብሎ ለማመን በቂ ምክንያት ሲኖር ያለፍርድ ቤት ማዘዣ ወደ ማንኛውም ሰው መሬት፣ ሕንፃ፣ ድንኳን፣ ተሽከርካሪ፣ የአየር መንኩራኩር ወይም ጀልባ ውስጥ የመግባትና የመፈተሽ እንዲሁም ሻንጣ ወይም እሽግ የመበርበር፤

፫/ ሕግን በመተላለፍ በይዞታ ሥር የተደረጉ የዱር እንስሳትና የዱር እንስሳት ውጤቶችን እንዲሁም ጥፋቱ የተፈጸመባቸውን መሣሪያዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮(፪) መሠረት እንዲወረሱ ለማድረግ እንዲቻል በቁጥጥር ሥር የማድረግና ሚኒስቴሩ ወይም የሚመለከተው የክልል አካል ባወጣው የመመዝገቢያ ቅጽ መሠረት ተገቢውን ደረሰኝ ሰጥቶ የመረከብ፤

፬/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፲፮ ድንጋጌዎች በመተላለፍ ጥፋት ሲፈጽም ያገኘውን ሰው ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ይዞ ለሚመለከተው ሕግ አስከባሪ አካል ማቅረብ፡፡

፭/ ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት።

4/ control and prevent incidents of wildlife diseases within and outside of conservation areas and inform the Ministry when the case is beyond their capacity;

5/ issue permits for the establishment of wildlife ranches and farming and supervise same;

6/ undertake the necessary study on wildlife causing threat to human life and property and take appropriate measure to minimize and prevent the threat, and report to the Ministry when the case is beyond their capacity;

7/ issue hunting permits to persons other than foreign tourists;

8/ issue permits to own, transfer and sale locally wildlife and wildlife products;

## 15. Powers and Duties of Wildlife Ant-Poaching Officers

A wildlife ant-poaching officer shall have the following powers:

1/ to require any person who is in possession of wildlife or wildlife products to show the permit authorizing such possession;

2/ to enter and search any private landholding, building, tent, vehicle, aircraft or boat as well as search bags or sealed items, without court order, where there are sufficient grounds to believe that wildlife or wildlife products are kept illegally;

3/ with a view to secure an order of confiscation pursuant to Article 16(2) of this Proclamation, to seize and takeover, upon issuing receipt in accordance with the format issued by the Ministry or the concerned regional organ, any wildlife or wildlife product which is a proceed of an offence as well as the weapon with which the offence has been committed;

4/ where a person is found committing an offence in violation of Article 16 of this Proclamation, to detain, without any court order, and handover him to the appropriate law enforcing body.

5/ Any person has the Obligation to collaborate in the implementation of this proclamation

## ፲፮. ቅጣት

፩/ በወንጀለኛ ሕግ መሠረት የበለጠ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፣

ሀ) ማንኛውም ሰው፣

(i) ሕገወጥ የዱር እንስሳት አደን ወይም ንግድ ድርጊት ከፈጸመ፣

(ii) በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ያልተፈቀዱ ተግባሮችን ካከና ወነ ወይም በማናቸውም አኳኋን በነዚሁ ላይ ጉዳት ካደረሰ፣ ወይም

(iii) የዱር እንስሳትን ወይም የዱር እንስሳት ውጤቶችን ያለፈቃድ ይዞ ከተገኘ፣

ከብር ፭ሺ በማያንስና ከብር ፴ሺ በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበይልጥ እስራት ወይም በሁለ ቱም ይቀጣል፡፡

ለ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም አዋጁን ለማስ ፈጸም የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ ሌሎች ጥፋቶችን የፈጸመ ማንኛውም ሰው ከብር ፭፻ በማያንስና ከብር ፫ሺ በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአንድ ወር በማያንስና ከስድስት ወር በማይበልጥ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ፍርድ ቤት ቅጣት ሲወስን ከቅጣቱ በተጨማሪ ከጥፋቱ የተገኘው የዱር እንስሳ ወይም የዱር እንስሳ ውጤት እንዲሁም ጥፋቱ የተፈጸመበት መሣሪያ ውርስ እንዲሆን ይወሰናል፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ ወይም የሚመለከተው የክልል አካል፣

ሀ) የተወረሰውን የዱር እንስሳ ወይም የዱር እን ስሳ ውጤት እንደአግባቡ መሸጥ፣ ለሳይንስ ተግባር፣ ለትምህርት ተቋም ማስተላለፍ ወይም ከጥቅም ውጭ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል፡፡

ለ) የተወረሰውን መሣሪያ እንደአግባቡ ለሚመለ ከተው መንግሥታዊ አካል ማስተላለፍ ወይም ከጥቅም ውጭ እንዲሆን ማድረግ፣ ይችላል፡፡

## ፲፯. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 16. Penalty

1/ Unless it entails higher penalty under the criminal law:

a) any person who:

( i) commits an act of illegal wildlife hunting or trade;

(ii) carries out unauthorized activities within wildlife conservation areas or causes, in whatever way, damage thereto; or

(iii) is found in possession of wildlife or wildlife products without having a permit;

shall be punished with fine not less than Birr 5000 and not exceeding Birr 30,000 or with imprisonment not less than one year and not exceeding five years or with both such fine and imprisonment.

(b) any person who commits other offences in violation of the provisions of this Proclamation or regulations or directives issued hereunder shall be punished with fine not less than Birr 500 and not exceeding Birr 3,000 or with imprisonment not less than one month and not exceeding six months or with both such fine and imprisonment.

2/ Where a court passes a sentence pursuant to Sub-Article (1) of this Article, it shall, in addition to the sentence, order the confiscation of the wildlife or wildlife products which are the proceeds of the offence together with the weapon with which the offence is committed.

3/ The Ministry or the concerned regional organ may, as appropriate:

(a) sale, transfer to a scientific purpose, to academic institution or destroy the confiscated wildlife or wildlife product;

(b) transfer to the appropriate government organs or destroy the confiscated weapon.

## 17. Power to Issue Regulations and Directives

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲፰. የተሻሩና ጸንተው የሚቆዩ ሕጎች

፩/ የሚከተሉት ሕጎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፤

ሀ) የደንና ዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት አዋጅ ቁጥር ፩፻፺፪/፲፱፻፸፪ /እንደተሻሻለ/፤

ለ) የዱር እንስሳት ጥበቃ ደንብ ቁጥር ፬፻፲፮/፲፱፻፷፬ /እንደተሻሻለ/፡፡

፪/ የሚከተሉት ሕጎች በዚህ አዋጅ መሠረት እንደወጡ ተቆጥረው የጸኑ ይሆናሉ፤

ሀ) የአዋሽ ብሔራዊ የዱር እንስሳት ጥበቃ ፓርክ ማቋቋሚያ ትዕዛዝ ቁጥር ፶፬/፲፱፻፷፩፤

ለ) የሰሜን ብሔራዊ የዱር እንስሳት ጥበቃ ፓርክ ማቋቋሚያ ትዕዛዝ ቁጥር ፶፱/፲፱፻፷፪፡፡

## ፲፱. ተፈጻሚ ስለማይሆኑ ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## ፳. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

2/ The Ministry may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued under Sub-Article (1) of this Article.

## 18. Repeal and Savings

1/ The following are hereby repealed:

(a) the Forestry and Wildlife Conservation and Development Proclamation No. 192/1980;

(b) the Wildlife Conservation Regulations No. 416/1972 (as amended).

2/ The following legislations shall be deemed to have been issued under this Proclamation and shall remain in force:

(a) the Awash National Park Establishment Order No. 54/1969;

(b) the Simien National Park Establishment Order No. 59/1970.

## 19. Inapplicable Laws

No law, regulation, directive or practice may, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable to matters provided for by this Proclamation.

## 20. Effective Date

This Proclamation shall come into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 7th day of June, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**